## ከጀግና ጋር እንቁም

አገሬ ስትጠፋ
እኔ አላይም ብሎ
በወገኑ ፍቅር
ልቡ እጅግ ተቃጥሎ
የአገር ጥሪ ሰምቶ
የሕዝቡን ስቃይ
ያለማወላወል
ፈጥኖ አለሁሽ ባይ
ስልቱን አውጥቶና
ከሕዝቡ ጋር መክሮ
የሰላምን ትግል
ከገጠር ጀምሮ
ባራቱ ማዕዘን
ሕዝብን አስተባብሮ
እርሱም ልምድን ቀስሞ
ወገን አስተምሮ
በሰፊው አደራጅቶ
ለትግል አብቅቶ
ተፈትኖ ያለፈው
ብዙ ሥራ ሰርቶ
ጀግናው እርሱ ነበር
የለም ሌላ ከቶ፡፡
በእግር በመኪና
በበቅሎ ተጭኖ
ቆላ ደጋ ወርዶ
ከሕዝቡ ጋር ሁኖ
ከደሃው ጋር በልቶ
ጎጆው ውስጥ ተኝቶ
በረሃ አቋርጦ
ወገኑን ጎብኝቶ
ችግሩን አዳምጦ
መፍትሔ አምጥቶ
በአንድነቱ ጎራ
ሁሉንም አካትቶ
በኢትዮጲያዊነቱ
ኮርቶና አኩርቶ
ቃል ገብቶ ለወገን
ወገንም ቃል ገብቶ
ታስሮ ተንገላቶ
ለመብቱ ተሟግቶ
በግንቦቱ አየነው
ለማሸነፍ በቅቶ፡፡
ጀግና መሪ ሲኖር
ሕዝቡም ይከተላል
አሁንም በሰፊው
ትግሉን አጠናክሯል
ከጀግና ጋር እንቁም
ትግሉ መስመር ይዟል
ድሉ መቼም አይቀር
ዘንድሮስ ይለያል፡፡

ግርማ ቢራቱ
ዊኒፔግ፡ ካናዳ

EthioLion.Com